# ለብቻ ከእግዚአብሔር ጋር የመሆን ጊዜ ።



ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻ መሆን ስትጀምር አስቀ
ድመህ ስለ አምላክነቱ አመስግነው ። ከዚያም ስላደረገ
ልህ ነገር ሁሉ የውለታ ምስጋና አቅርብለት ። ሊያደር
ግልህ ስላለው ነገርም አመስግነው ። ስላደረግሽው አን
ዳች ጥፋት እንኳ ሳይቀር ተናዘዝ ። እርሱም ይቅር ይላ
ሃል ። ፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፡ ፱ ስለ ቤተሰብህና ስለ ጓደኞችህ
ሁሉ ጸልይ ። ፊልጵስዩስ ፪ ፡ ፬ ። ኢየሱስም አዳኙ
እንዲሆን ለምትመኝለት በአንድ በምታውቀው ሰው
ልብ እግዚአብሔር እንዲሠራ ጠይቀው ። ስለ አዲስ
አማኞችም ጸልይ ። ስለ መንግሥት ባለሥልጣኖች ፣
ስለ መጋቢህና ስለ ጸሎት ቤትህ ጸልይ ። እየጸለይክ
ስለ እግዚአብሔር እራሱ ለሌሎች ደግሞ እንድትጸልይ
ይመራሃል ።

ስለ ራስህም ጸልይ ። በየዕለቱ እንዲመራህ ፣ በገጠ
መህ ማንኛውም እክል እንዲረዳህ ፈቃዱንም ማድረግ
እንድትችል እንዲያግዝህ እርሱንም ለማገልገል ዕድል
እንዲሰጥህ ጠይቀው ። ጸሎትህንም እንደመለሰልህ
እመን ። ስለመለሰልህም አመስግነው ።

ቃሉን በሐሳብህ ማሰላሰልና ከእርሱ ጋር በጸሎት
መነጋገርህ ከአምላክህ ጋር በጣም ወደተቀራረበ አንድ
ነት ወይም ኅብረት ያመጣሃል ። ይህንንም ለማድረግ
ምቹ ጊዜና ስፍራ ማግኘቱ ቀላል አይደለም ። ጊዜውን
እራስህ መወሰን ይኖርብሃል ። ይህን እያደረግህ ሳለ
ለእርሱ ያለህ ፍቅር እያደገ ይሄዳል ። እርሱም ደግሞ
ከአንተ ጋር ለብቻ ለመገናኘት እንደሚጠባበቅ ማስታወስ
አለብህ ።

S.I.M. PRESS